# ለኤፒዱራል የምጥ ሕመም ማስታገሻ

## ኤፒዱራል ምንድ ነው?

ኤፒዱራል የምጥ ህመም ኣነስተኛ እንዲሆን የሚጠቅም የህመም ማስታገሻ ዓይነት ነው።

አንድ ሀኪም ኤፒዱራል ካቴተር በመባል የሚታወቀውን አነስተኛ የፕላስቲክ ቱቦ አከርካሪዎ አቅራቢያ ላይ ያስቀምጣል፤ ይህ ቱቦ (ኤፒዱራል ስፔስ) ተብሎ ይጠራል። በአከርካሪ ያሉ የስቃይ ነርቮችን ለመከልክል የሕመም አስታጋሽ መድሃኒቶች በካቴተር አማካኝነት ይሰጣሉ። ህጻኑን እስኪወልዱ ድረስ ህመም ሊያስታግስ ይችላል።

በምጥና በወሊድ ወቅት የሚከሰት ህመምን ለማስታገስ በጣም ውጤታማ ዘዴ ኤፒዱራል ነው።

## አንድ ኤፒደርል ምን ጥቅሞች አሉት?

ልጅዎ በኃይል ወይም በድንገተኛ ጊዜ በቀዶ ጥገና/ሲዛሪያን አማካኝነት መውለድ ካስፈለገው ኤፒዱራል የህክምና ሂደቱን በፍጥነት ለማስጀመር ሊረዳው ይችላል።

ኤፒዱራል የተደረገልዎት ከሆነ በቀዶ ጥገና/ሲዛሪያን ወቅት ልጅዎን ሲወልዱ ኣጠቃላይ ማደንዘዣ መውሰድ ኣያስፈልግዎትም፤ ስለዚህ የልጅዎት መውለድ የሚከናወነው ነቅተው ነው ማለት ነው።

ኤፒዱራል በህጻን ልጅዎ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ እንደማያሳድር ወይም በድንገተኛ የቀዶ ጥገና/ሴዛሪያን የማድርግ አጋጣሚ እንደማይጨምረው ጥናቶች ያመለክታሉ።

## የኤፒዱራል ካቴተር የሚቀመጠው እንዴት ነው?

የማደንዘዣ ባለሙያ በሰውነትዎ ላይ ኤፒዱራልን ያስቀምጣል። ይህ ወደ 20 ደቂቃዎች ይወስዳል።

- በሰውነትዎ ፈሳሽ እንዲኖር በእጅዎ ወይም በእጅ ግንድዎ ውስጥ የሚንጠባጠብ ፈሳሽ ይቀመጥልዎታል።
- ለቀዶ ህክምናው በጎን ይተኛሉ አሊያም ይቀመጣሉ።
- ጀርባዎን ለማጽዳት ቀዝቃዛ የቁስል መጥረጊያ ቅልቅል ጥቅም ላይ ይውላል።
- በጀርባዎ ላይ ያለውን ቆዳ ለማደንዘዝ በአካባቢወ የማደንዘዣ መርፌ ይወጉታል።
- ኤፒዱራል በሚገባበት ጊዜ ጀርባዎ ላይ የጫና ግፊት ሊሰማዎት ይችላል። ቀጥ ብሎ መቆየቱ ለቀዶ ህክምናው በተሳካ ሁኔታ እንዲቀጥልና የጎንዮሽ ጉዳት ሊያስከትል የሚችለውን አጋጣሚ ለመቀነስ ይረዳዋል።
- የኤፒዱራል ካቴተር በሚቀመጥበት ጊዜ በጀርባዎ ወይም በእግሮችዎ ላይ ስቅቅ የሚል የመንቀጥቀጥ ስሜት ይሰማዎት ይሆናል። ይህ ኣደገኛ ኣይደለም።
- መርፌው ከወጣ በኋላ የኤፒዱራል ካቴተር ደህንነቱ በተጠበቀ መልክ ከቆዳዎ ጋር በቴፕ ይጣበቃል።
- ሰመመን ሰጪ መድሃኒቶች በካቴተር በኩል የሚያልፉ ሲሆን ተግባራዊ ለመሆን ከ10 እስከ 20 ደቂቃ ገደማ ይወስዳሉ።

## ኤፒድራል በእርስዎ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

ኤፒዱራል የእርስዎ እግሮች ከባድ ስሜት እንዲሰማቸው ሊያደርግ ስለሚችል በአልጋዎ ላይ መቆየት ያስፈልግዎታል።

በተጨማሪም ፊኛዎ ሲሞላ ለመረዳት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ በመሆኑም የሽንት ካቴተር ያስፈልግዎታል።

የመንቀጠቀጠት፣ የማሳከክ ወይም ሞቅ ያለ ስሜት ሊያጋጥምዎ ይችላል።

ኤፒዱራል አልፎ አልፎ  የምጥ ጊዜ ሊያራዝም ወይም ልጅዎን ለመውለድ ፎርሴፕን መጠቀም (መቀስ መሳይ የሃኪም እቃ) አስፈላጊነት ከፍ ሊያደርግ ይችላል።

በተጨማሪም በልጅዎ የልብ ትርታ ላይ ለውጥ ሊያስከትል ይችላል። ለማንኛውም ለውጥ እርስዎንም ሆነ ልጅዎን በቅርበት እንከታተላለን።

## ስጋቶቹ ምንድን ናቸው?

ኤፒዱራሎች ምንም ጉዳት የማያስከትል ቢሆንም የጎንዮሽ ጉዳት ሊያስከትል ይችላሉ።

ከተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች መካከል የደም ግፊት መቀነስና በተቆራረጠ መልክ የቧንቧ የመዘጋጋት ሁኔታ በእኛ ክትትል በኩል ህክምና ማግኘት ይቻላል።

ብዙም ከማያጋጥሙ ችግሮች መካከል  ከባድ ራስ ምታት አንዱ ነው።

በጣም ሳት ብለው ከሚከሰቱ የጤና መወሳሰቦች መካከል ጊዜያዊ የነርብ ጉዳት፣ ብክለት/ኢንፌክሽን፣ በጣም ከፍተኛ የሆነ የኤፒዶራል መዘጋትና የኤፒዱራል ደም መዘጋት ይገኙበታል። ከባድ አካላዊ ጉዳት ወይም ሽባነት በጣም ያልተለመደ ነገር ነው።

## ለበለጠ መረጃ

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ከእርስዎ ማህጸን ባለሙያ ወይም አዋላጅ ጋር መነጋገር ይችላሉ። ከአንድ ማደንዛዣ ባለሙያ ጋር እንዲነጋገሩ ሊያቀናጅልዎት ይችላሉ።

### አጣዳፊ የህመም አገልግሎት

### ሮያል የሴቶች ሆስፒታል

ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 8 (am) እስከ ከስዓት በኋላ 4 (pm)
ስልክ: (03) 8345 2389

## አስተርጓሚ ይፈልጋሉን?

ካስፈለግዎ አስተርጓሚ እንዲቀርብ መጠየቅ ይችላሉ።

## በቤተሰብ ሁከት ፈጠራ ድጋፍ

**1800 Respect National Helpline**

የጾታ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ወይም በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።
ቀን ወይም ማታ በማንኛውም ጊዜ መደወል ይችላሉ።
1800 737 732
1800respect.org.au

**የእኔ ኣይደለም ስለማለት/Disclaimer:** ይህ ሓቃዊ ጽሁፋዊ ወረቀት አጠቃላይ መረጃ ብቻ ያቀርባል። ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የጤና እንክብካቤ በተመለከተ ግልጽ የሆነ ምክር ለማግኘት ከጤና ባለሞያዎችዎ ምክር መጠየቅ ይኖርብዎታል። ሮያል የሴቶች ሆስፒታል የጤና ባለሙያ ከማየት ይልቅ በዚህ ሓቃዊ ጽሁፍ ወረቀት ላይ በመመካትዎ ምክንያት ለሚደርስብዎት ኪሳራ ወይም ጉዳት ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይቀበልም። እርስዎም ሆኑ ልጅዎ አጣዳፊ የሆነ ህክምና እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እባክዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ህክምና ክፍል ያነጋግሩ።
© The Royal Women’s Hospital 2025